# የቆላስይስ እና ኤፌሶን ጥናት 2

**የጥናት ክፍል፡ ኤፌሶን 2፡1-22 ቆላስይስ 1፡13-22 ቆላ 2፡9-15**

በዛሬው ጥናታችን ያለክርስቶስ ስንኖር የኖርንበት ኑሮ ምን ይመስል እንደነበርና እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ምን እንዳደረገልን ይህ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ያደረገውን ሥራና በክርስቶስ በማመናችን የተደረጉልንን ነገሮች እናጠናለን፡፡

**ርዕስ፡** <u>በክርስቶስ መሆንና ያለክርስቶስ መሆን</u>

እስካሁን ካጠናናቸው ክፍሎች ጨምሮ በሁለቱ መፃህፍት ውስጥ ጳውሎስ በተደጋጋሚ የተጠቀመባቸው ቃላትን ፈልጋችሁ ለማገኘት ሞክሩ፡፡

**3ቱ ጊዜያት**

| ዓለም ሳይፈጠር | ያሁኑ ዘመን | የሚመጣው ዓለም |
|---|---|---|
| አስቀድሞ ያዘጋጀው | መልካምን ስራ ለማድረግ | የሚመጡ ዘመናት |
| | | |
| | | |
| | | |

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሙታን ነበራችሁ ሲል ሞት ማለት ምንድነው ማንስ ገደላቸው?
2. እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ እኛን ከሞት ለማዳን ያደረጉትን ተነጋገሩ፡፡
3. የክርስቶስን ማንነት እንዴት ተብራራ?
4. ያለክርስቶስ ስንኖር የምንጠራባቸው ስሞች ምን ምን ነበር? ከ15 በላይ ተዘርዝረዋል፡፡
5. በክርስቶስ የሆኑልን ነገሮችን ዘርዝሩ 12 በላይ ተዘርዝረዋል፡፡ ከነዚህም በጣም ያስደነቃችሁ ዬቱ ነው?
6. ከአነዚህ ከተዘረዘሩት የኃጢአት ውጤቶች አላቅቆን የክርስቶስ አካል ሲያደርገን የእግዚአብሔር ምህረትን ፀጋውን እንዴት አስተዋላችሁ?
7. ሞታችኋል/ተቀብራችኋል/ተነስታችኋል/ተቀምጣችኋል የሚሉ ቃላት እንዴት ትረዳላችሁ?
8. ፍፁም የሚሆን ሰው ማቅረብ ወይም ፍፁም ሆኖ መቅረብ እንዴት ይቻላል?

### መተግበር (Application)

- ወደ ጌታ ስንመጣ ያለክርስቶስ መሆናችሁ ምን ያክል ተረድታችሁ ነው?
- ዛሬ በክርስቶስ በመሆን ብቻ የተደረጉሉንን ምን ያህል እናስተውላለን?
- ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ምን ያክል አስተማራችሁ?

ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥ ኤፌሶን 2፡ 4-5
እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ፤ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፤ ቆላ 2፡13